# በፅልመተኞች ሴራ የማይደበዝዘው ሃይማኖታዊ መቻቻላችን

መሐመድ አብዲ - ከባምቢስ

ፍንትው ያለ ብርሃን ያስፈራቸዋል፡፡ ወገግ ብሎ በሚታይ ነባራዊ ሁኔታ ውስጥ ዓይናቸውን ከመግለጥ ይልቅ፤ ድቅድቅ ጨለማን እንደ እልፍኝ አዳራሽ በመቁጠር ያልተፃፈን ድርሳን እያነበነቡ ይንጎራደዳሉ፡፡ ጭላጭል ሰለማዊ ብርሃን የፅልመት ሴራቸውን የሚያናጥብባቸው እየመሰላቸውም፤ ያልተባለ ጉዳይን ለመቀመር የአመጽን ዶሴ እየመዘዙ ይተነብያሉ አሊያም ያስተነብያሉ፡፡ እናም ከእውነታው ቅኝት እያፈነገጡ በተቃራኒው መንገድ ይዘምራሉ፤ ያስዘምራሉ፡፡

ዝማሬያቸውን የሚያስተጋቡበት ግጥም ሃይማኖታዊም ይሁን ዓለማዊ ምጣኔ የሌለው ከመሆኑም በላይ፣ እውነትን ፈጽሞ አያውቀውም፡፡ የልፈፋቸው ልኬት የሚወሰነው ‘ምን ያህል ከነባራዊው ሃቅ አፈንግጧል?’ ብሎ በሚገመት “የቢሆን” ስሌት ክስተቶችን በማራገብ ብቃቱ ላይ ተመርኩዞ ነው፡፡ ጽልመተኞቹ ትናንትን ወደ ኋላ ዞር ብለው አያዩም፤ ነገንም የሚያልሙት ከጨለማ ዳንኪራቸው አኳያ ነው፡፡ይሁን እንጂ ነገንም ቢሆን በቅጡ አያውቁትም፡፡ ብቻ ለዛሬ የሚሆን አዲስ ክስተት ካለ እርሱን አንጠልጥሎ መሮጥ ነው– የፖለቲካ ቅኝታቸው አልፋና ኦሜጋ፡፡

እርግጥ ውድ አንባቢዎቼ እነዚህን ጽልመተኞች ከባህሪያቸው አኳያ በመግቢያዬ ላይ ያነሳኋቸው ያለ ምክንያት አለመሆኑን እንደትገነዘቡልኝ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ አዎ! ጽልመተኞቹ ከመሰንበቻው በሃይማኖት አክራሪነት ሽፋን ተከልለው በሀገራችን ለዘመናት ሰፍኖ የኖረውን ሃይማኖታዊ መቻቻላችንን ለማደብዘዝ ሲሯሯጡ መመልከቴ ነው– ብዕሬን ከወረቀት ጋር እንዳገናኝ ያደረገኝ፡፡

እንደ እውነቱ ከሆነ እጅግ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው፣ ነገር ግን ራሳቸውን እንደ ትክክለኛ አማኝ በመቁጠር በሙስሊሙም ይሁን በክርስትና ሃይማኖቶች ውስጥ “በሃሰተኛ መሲህነት” የሚርመሰመሱት እነዚህ ወገኖች፤ ስለምን በሀገራችን ውስጥ ያለውን ሃይማኖታዊ መከባበርና መፈቃቀድ ለመበረዝ እንደሚሯሯጡ ግልጽ ነው፡፡ ይኸውም የሃይማኖት ጉዳይ የሰዎችን ስሜት በቀላሉ የሚኮረኩር በመሆኑ፤ተግባሩ ውስጥ ሆኖ ሙስሊሙንም ሆነ ክርስቲያኑን በቀላሉ ወደ ማይፈለግ የጥላቻና የአመጽ አቅጣጫ በመምራት በቀላሉ የፖለቲካዊ ስልጣን ግብን ማሳካት ይቻላል ብለው ስለሚያስቡ ነው፡፡

ዳሩ ግን የኢትዮጵያ ህዝቦች ከብዙዎቹ የዓለማችን ህዝቦች የክርስትናንም ይሁን የእስልምና እምነቶችን አስቀድመው የተቀበሉ ብቻ ሳይሆኑ፤ የተለያዩ ሁለገባዊ አስተሳሰቦችን ፈጥረው የመቻቻልና የመከባበር ባህልን ያዳበሩ ለመሆናቸው የታሪክ ድርሳናት ይመሰክራሉ፡፡ በዚህም የሃይማኖት ብዙህነትን ከነበራቸው አርቆ አስተዋይነት አኳያ ሲያስተናግዱ የኖሩና ጠንካራ አንድነትና ውህደት ያላቸው ኩሩ ህዝቦች መሆናቸውን አስመስክረዋል፡፡

ምንም እንኳን ባለፉት ሥርዓቶች በየጊዜው የተነሱት ነገስታትና ሱልጣኖች አንዳቸው በሌላኛው ላይ የበላይነትን ለመቀዳጀት አልፎ አልፎ በሃይማኖት ጦርነት መልክ ፖለቲካዊ ፍልሚያዎች ቢያካሂዱም እንዲሁም በርካታ ዜጎች በሃይማኖታቸው ምክንያት እንደ ሁለተኛ  ዜጋ ቢቆጠሩም፤ የሀገራችን ህዝቦች ከነበራቸው ጠንካራ አብሮ የመኖርና የመከባበር ባህል አኳያ ሃይማኖታዊ መቻቻላቸውን ጠብቀው "አንተ ትብስ፣ አንቺ ትብሽ" በማለት አብረው መኖራቸው ዓለም የመሰከረለት ዕውነታ ነው፡፡

ይህ ዘመን የማይሽረው ሃቅ የትናንት ታሪካችን፣ የዛሬና የነገ ደግሞ የማንነታችን መገለጫ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ህዝቦች የሃይማኖት እኩልነትና የእምነት ነጻነት ፈጽመው በማይታወቁባቸው በእነዚያ ዘመናት ተከባብረው በአንድነት ዘልቀው ዛሬ ላይ ደርሰዋል፡፡ ላለፉት 21 ዓመታት የሀገራችን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ህገ - መንግስቱ በሰጣቸው ዋስትና መሰረት የአንደኛው ሃይማኖት ከሌላኛው ሳይበላለጥ እንዲሁም ያሻቸውን ዓይነት እምነት በማምለክ ላይ ይገኛሉ፡፡

እናም ባለፉት ሥርዓቶች ሃይማኖታዊ ነጻነታቸውን የተገፈፉት የኢትዮጵያ ህዝቦች ተከባብረው ከኖሩ፤ ዛሬ ላይ በእኩልነትና በነጻነት እምነታቸውን እያመለኩ የቀድሞ መቻቻላቸውንና መከባበራቸውን የሚተውበት አንዳችም ምክንያት ሊኖር አይችልም፡፡ ታዲያ ይህ የህዝቦች ተምሳሌታዊነት ለሌሎች ሀገሮች አርአያ መሆን የሚችል ባህል መሆኑ አያጠራጥርም። በመሆኑም ዕውነታው በአክራሪነት ጎራ ተሰልፈው ክርስቲያኑንም ሆነ ሙስሊሙን ማህብረሰብ ለመበጥበጥ ቀን ከለሊት ለሚባዝኑ ጽንፈኞች ቦታ የሚሰጥ አይደለም፡፡

ታዲያ ይህን ሃቅ "በጽልመት ነብያትነት" ተሰልፈው ህዝበ-ክርስቲያኑንና ሙስሊሙን እኩይ ሴራን እየሸረቡ በማጋጨት ፖለቲካዊ ትርፍ ለማግኘት የሚሯሯጡት ወገኖች በግልጽ ሊረዱት የሚገባ ይመስለኛል፡፡ምክንያቱም የሀገራችን ህዝቦች ሃይማኖታዊ የአብሮነት ኑሮ "ነብር ዥንጉርጉርነቱን እንደማይቀይር ሁሉ፤ ኢትዮጵያዊም ማንነቱን አይቀይርም" ተብሎ በቅዱስ መጽሐፉ  ላይ እንደተገለጸው ዓይነት በመሆኑ ነው፡፡

ትናንት ልጁን ሲድር ሁለት በሬ አርዶ፣ እና ሁለት ድንኳን ጥሎ አንዱን ለክርስቲያን ሌላኛውን ለሙስሊም ጎረቤቱ ሲያበላ የነበረ የክርስትና እምነት ተከታይ፤ ዛሬ ባህሉንና ወጉን ቀይሮ ማንነቱን ሊሽር አይችልም፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታም በረመዷን ፆም ፍቺ ወቅት በዓሉን ሲያከብር ሁለት ድስት በመስራት አንዱን ለሙስሊም ሌላኛውን ደግሞ  ለክርስቲያን ጎረቤቱ የሚያዘጋጀው የኢስላም እምነት ተከታይ፤ ይህን ያደገበትን ባህላዊ ትውፊት ትቶ አዲስና በማንኛውም መስፈርት ተቀባይነት የማይኖረውን የጽንፈኞችን "ሃይማኖታዊ ፖለቲከኝነት" ሊይዝ የሚችልበት ኑባሬያዊ ተፈጥሮ የለውም።

ይሁን እንጂ ፅልመተኞቹ ይህን ሃይማኖታዊ መከባበርና መቻቻል ለመናድ ያልፈነቀሉት የሴራ ቋጥኝ አለ ለማለት አያስደፍርም፡፡ እስቲ ለውድ አንባቢዎቼ ግንዛቤ ይረዳ ዘንድ ጥቂት የእውነታ ሰበዞችን ልምዘዝ፡፡ … ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሃይማኖትን ሽፋን ያደረጉ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች በክርስትናም ይሁን በእስልምና እምነቶች ውስጥ ብቅ ጥልም እያሉ መታየታቸው ዛሬ ላይ ያለንበት ዕውነታ ነው፡፡ ሃይማኖቶቹን

ተገን በማድረግ ገደቡን የሳተ ቅስቀሳና ማነሳሳት ሲካሄድ መቆየቱም ግፋ ቢል የአራትና አምስት ዓመት ትውስታችን ቢሆን ነው፡፡

ታዲያ “ጠብ ያለሽ በዳቦ” በሚል ሰበብ በእነዚህ ዓመታት በጽንፈኞች አማካኝነት በክርስትናው ሃይማኖት ውስጥ “ኢትዮጵያ የክርስቲያኖች ደሴት ናት” የሚልና ከሀገሪቱ ህዝቦች ነባር የመቻቻል ባህል ያፈነገጠ መፈክር በአደባባይ ይዞ እስከ መውጣት ተደርሶ ነበር፡፡

ይህ በአብዛኛው የክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ ፈጽሞ ተቀባይነት የሌለውና የሌሎች ሃይማኖት ምዕመናንን መብት በይፋ የሚጋፋው አስተሳሰብ በዚህ ተግባሩ ብቻ ያበቃ አልነበረም፡፡ አክራሪዎቹ ጥቂት ያሳሳቷቸውን ተከታዮቻቸውን በማሰለፍ ይህንኑ “የክርስቲያን ደሴትነት” መፈክርን በቲሸርት ላይ አጽፈው ሲዘሩ እንደነበር ሁላችንም የምንዘነጋው አይደለም፡፡ ሆኖም እንዲህ ዓይነቱ ክስተት ሃይማኖቱን ብቻ ለመከታተል ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚሄደውን የእምነቱን ተከታይ ማስቆጣቱ አልቀረም፡፡ ምዕመኑ በማይፈልገው መልኩ በቪሲዲና ዲቪዲ እየተቀረጸ በገሃድ የሚተላለፈው አፍራሽ ፖለቲካዊ ቅስቀሳም የጽልመተኞቹ ሴራ አንዱ ስልት ነበር፡፡ ይሁንና ህዝበ ክርስቲያኑ ድርጊቱ የጠብ ጫሪነት ፍላጎት እንጂ ሃይማኖታዊ አለመሆኑን ስለሚገነዘብ የጽንፈኝነት አስተሳሰቡን “ጆሮ ዳባ ልበስ” በማለት እነሆ ከሙስሊም ወንድሞቹ ጋር በሠላምና በመፈቃቀር እየኖረ ነው፡፡

ጽልመተኞቹ በእስልምናው ሃይማኖት ውስጥም ህዝበ - ሙስሊሙን አሳስቶ ወደ ግጭት ያስገባልናል ያሉትን የሴራ ዱለታ ከመከወን ወደ ኋላ አላሉም፡፡ እነዚህ ወገኖች በል ሲላቸው ክርስትናን እና ሌሎች እምነቶችን ይዘልፋሉ፡፡ ሲያሻቸው ደግሞ በጋዜጦች፣ በመጽሔቶች እና በመጽሐፍቶች እንዲሁም በቪሲዲና ዲቪዲ አማካኝነት የሚሰራጩና የተቀረጹ መረን የለቀቁ አደገኛ መልዕክቶችን በመጠቀም ሙስሊሙን ምዕመን ያደናግርልናል ያሉትን የግጭት አካሄድ ተጠቅመዋል። (በተለያዩ ጋዜጦች ላይ መጅሊስንና ሃይማኖታዊ ምርጫን አስመልክቶ የበሬ ወለደ ድርሰትና ሌሎች ልፈፋዎችን የሚያስተጋቡትን ነውጠኞችን ያስታውሷል!)

ከዚህ አልፎ ተርፎም እነዚህ ወገኖች በአሁኑ ወቅት የኢስላም እምነት ሙሉ ለሙሉ በህገ -መንግስቱ መብትና ነጻነት የተሰጠው መሆኑን እያወቁ፤ ባለፉት ስርዓቶች በሃይማኖቱ ላይ ሲደርስ የነበረውን በደል ዛሬ ላይ የተፈጸመ ያህል የማራገብ ስራዎችን ሲያከናውኑ ነበር፡፡ ለዚህም የደርግ ባለሚሎችንና የጎዳና ላይ ነውጥ አቀጣጣይ ተላላኪዎች የነበሩ “ጋዜጠኞች” እና “ፀሐፊዎችን” ከያሉበት ቦታ በዘመቻ መልክ በማሰስ የጥላቻ ድርሳን እንዲያነበንቡ አድርገዋል፡፡ ከዚህ ባሻገርም እነዚህ የከሰሩ ጽንፈኛ ፖለቲከኞች ሃይማኖትና ትምህርትን ለመነጣጠል በግልጽ በህገ -መንግስቱ ላይ የተቀመጠውን ድንጋጌ ለመጣስ በከፍተኛ ተቋማት ውስጥ መስጊድ እንዲሰራ ከመጠየቅ ጀምሮ፣ በአልባሳት ጉዳይም እሰጥ አገባ በመፍጠር ሰላማዊውን የትምህርት ምህዳር ለማወክ ተንቀሳቅሰዋል፡፡

ይሁን እንጂ አብዛኛው ህዝበ -ሙስሊም የፅንፈኞቹ አካሄድ ከፖለቲካዊ ይዘት በስተቀር አንዳችም ጠብ የሚል ሃይማኖታዊ እሳቤና ይዘት የሌለው መሆኑን በመረዳቱ ለዘመናት አብሮት ከኖረው ክርስቲያን ወንድሞቹ ጋር በሠላም መኖሩን ቀጥሏል፡፡ ለምን ቢሉ፤ ላለፉት በርካታ ዓመታት በተለያዩ ማህበራዊ

መሰተጋብሮች የተሳሰሩት የሀገራችን ህዝቦች በጽልመተኞች እና በአክራሪዎች ሃይማኖታዊ በሚመስል ፖለቲከዊ ዳንኪራ የቁርኝት ድራቸውን መበጠስ ስለማይቻላቸው ነው፡፡

ምንም እንኳን በሁለቱም ሃይማኖት ውስጥ በከሰሩ ፖለቲከኞች አማካኝነት ይቀነባበሩ የነበሩት ግጭት የመቀስቀስ ሙከራዎች ዋነኛ ግባቸው ሀገራችን ውስጥ ሰላምና መረጋጋት የሌለ በማስመሰል ገጽታችን እንዲበላሽ ማድረግ ቢሆንም፣ ይህ ህልማቸው በኢትዮጵያ ህዝቦች ሰላም ወዳድነት ብሎም በመንግስታችን የሰከነና በሳል አመራር ዕውን ሊሆን አልቻለም፡፡ እናም የጽንፈኞቹ የጥፋት መለከት በክርስትናም ይሁን በእስልምና ሃይማኖቶች ውስጥ ሊነፋ ቢሞከርም፣ "የጽልመት ነብያቱ" ላለፉት 21 ዓመታት የሀገራችን ህገ - መንግስታዊ ስርዓት ለግጭት ቦታ ሰጥቶ የማያውቅ መሆኑን መገንዘብ ይኖርባቸው ነበር፡፡

ማንኛውም የዚህ ጽሑፍ አንባቢ እንደሚያውቀው፣ የሀገራችንን ዴሞክራሲያዊና ልማታዊ ስርዓት ለየት የሚያደርገው አንድ ወሳኝ ነጥብ ቢኖር፣ የኢፌዴሪ መንግስት በህገ -መንግስቱ ላይ የሰፈሩ መሰረታዊ መብቶችና ነጻነቶች ተግባራዊ እንዲሆኑ ከፍተኛ ጥረት እያደረገ መሆኑ ነው፡፡ በህገ -መንግስቱ ውስጥ ህጋዊ ከላላ ከተሰጣቸው ጉዳዮች መካከል በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሱት የእምነት ነጻነትና የሃይማኖት እኩልነት በመሆናቸው፣ እነዚህን መብቶች ሳይሸራረፉ ገቢራዊ ለማድረግ መንግስት ያልተቆጠበ ጥረት አድርጓል፡፡

የየትኛውም እምነት ተከታይ ያለማንም አስገዳጅነት በመረጠው ሃይማኖት እንዲመራ፣ ሃይማኖታዊ ግዴታውን ያለማንም ጣልቃ ገብነት እንዲፈጸም እንዲሁም መንግስትና ሃይማኖት ብሎም ሃይማኖትና የትምህርት ተቋማት ተነጣጥለው ተግባራቸውን እንዲከውኑ በማድረግ ረገድ ህገ - መንግስታዊ ድንጋጌው ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ በተግባር እንዲተረጎም አድርጓል፡፡ ጽንፈኞቹ ለብሶት ማራገቢያነት በሌለ ተጨባጭ ምህዳር የሚያነሷቸውና ባለፉት ስርዓቶች የሚከተሏቸው የሃይማኖት ጭቆናዎች እና የፍትህ መጓደሎች እንዲወገዱ በማድረግ ረገድም ግዙፍ ቦታ የሚሰጠው ርምጃ በመንግስት በኩል ተወስዷል፡፡

ከዚህ ጎን ለጎንም ባለፉት 21 ዓመታት ሁሉም ሃይማኖቶች አምልኮአቸውን የሚፈጽሙባቸው የእምነት ቦታዎች ከመስፋፋታቸው በተጨማሪ፣ የመቻቻል ባህላችን ማሳያ የሆኑት የሃይማኖት በዓላት ክብደት በሚሰጣቸው ሁኔታ እንዲከበሩ አስፈላጊ የሚባሉ ጉዳዮች ተመቻችተዋል፡፡ ታዲያ እነዚህ የሃይማኖትት እኩልነትን በተግባር ለመተርጎም የተከናወኑ ሃቆች ሀገራችን ውስጥ በማንኛውም እምነት ተከታይ ዘንድ ነባሩን የመቻቻል ባህል ይበልጥ ያሰፉና ያረጋገጡ እንጂ፣ ለግጭት በር የሚከፍቱ ክንዋኔዎች አለመሆናቸውን መገንዘብ ያሻል፡፡ በመሆኑም በዚህ የመቻቻልና ተፈቃቅሮ የመኖር ነባራዊ ምህዳር ውስጥ የጽንፈኞቹ የአመጽ ድቤ መቺነት የትም የሚያደርስ ሊሆን አይችልም፡፡

በዚህ ጽሑፍ አቅራቢ እምነት፣ ይህን የሀገራችንን የመቻቻል ሃይማኖታዊ ባህል ለማጉደፍ በኦርቶዶክስም ይሁን በእስልምና እምነቶች ውስጥ ሰርገው በመግባት ሁከትና ብጥብጥ ለመቀስቀስ የሚሞክሩ ወገኖች ተቋማቱን የፖለቲካ አጀንዳ ማስፈጸሚያ ማድረግ የሚፈልጉ ናቸው፡፡ እነዚህ ኃይሎች በሀገር ውስጥ

የከሰረ የፖለቲካ አጀንዳን ብቻ የሚያራምዱ አይደሉም፡፡ በጎረቤት ሀገር ካሉ አክራሪዎች ጋርም ንክኪ ያላቸውም መሆኑን ጠቋሚ ማሳያዎችን መጥቀስ ይቻላል፡፡

እንደሚታወቀው ባለፉት ጥቂት ዓመታት በሶማሊያ ፅንፈኝነትን የሚያራምዱ አክራሪዎች በአቋም ደረጃ አፍሪካን ከምስራቅ እስከ ምዕራብ፣ ከሰሜን እስከ ደቡብ ዋልታዎቿ ድረስ በእስልምና ሃይማኖት እናጠምቃታለን ሲሉ ከርመዋል። ይህም የትስስሩ እንድ አመላካች ጉዳይ ሆኖ ሊወሰድ የሚችል ነው፡፡ በመሆኑም በሀገራችን በሃይማኖት ሽፋን ግጭትን የመቀስቀስ ፍላጎት አባዜ በሌላ ገጽታው የራሳቸው አጀንዳ ያላቸው የውጭ አክራሪዎች እጅ ያለበት መሆኑን ያመላክታል፡፡

በክርስትናው እምነትም ቢሆን ከዚህ የተለየ ሁኔታ አይስተዋልም፡፡ አንዳንድ የውጭው ዓለም የክርስትና እምነት አክራሪዎች "ሀገራችን የክርስቲያን ደሴት ትሆናለች" በሚሉት ጥቂት የሀገር ውስጥ ጽንፈኞች ላይ የራሳቸውን አሻራ ማሳረፋቸው የሚቀር አይመስለኝም፡፡ ለዚህም በአንድም ይሁን በሌላ መልኩ የሀገራችንን ነጻ ዕድገትና ግስጋሴን የማይፈልጉ የውጭ ኃይሎችና በሃይማኖት ሽፋን ተጠልለው ባህር ማዶ ቁጭ ብለው የፖለቲካ አጀንዳን ማራገብ የሚፈልጉ እንደ ግንቦት ሰባትና ኢሳት ያሉ ፀረ - ኢትዮጵያ ኃይሎች ተጠቃሽና እጃቸው ያለበት መሆኑ አይካድም፡፡ በየሚዲያው ውስጥ የተሰገሰጉ የደርግ እና የተለያዩ ትምክህተኛ ኃይሎች ቅሪቶችም በእነዚሁ ኃይሎች ዙሪያ ተኮልኩለው "ጉሮ ወሸባዬ" እያሉ ወሬ በማዳመቅ የሚያራግቡ ናቸው፡፡

እንግዲህ የእነዚህ ጥቂት ኃይሎች ግንባር ቀደም ግብ ፖለቲካ መሆኑን ከተግባባን ዘንዳ፤ 'አብዛኛው ምዕመን አሁን እየተከተለ ያለውን ነባሩን የመቻቻልና ተከባብሮ በተድላና በፍሰሐ የመኖር ባህሉን እንደምን ሳይደበዝዝ ማስቀጠል ይችላል?' የሚል ጥያቄ ማንሳት ተገቢ ይመስለኛል፡፡ እርግጥ የዚህ ጥያቄ ምላሽ በሁሉም ሃይማኖቶች ምዕመናን እጅ ያለ ነው፡፡ ምክንያቱም በፍቅርና በአንድነት ተከባብሮ የሚኖረው የክርስትናም ይሁን የእስልምና እምነት ተከታይ በውስጡ ያሉትንና ሃይማኖትን እንደ ግርዶሽ የሚጠቀሙ ትናንሽ ሐሰተኛ መሲሆችን ስለሚያውቃቸው ነው፡፡ በመሆኑም የእያንዳንዱ እምነት ተከታይ ለዘመናት የዘለቀውን መቻቻላችንን ለማቆርፌድ የተሰለፉ ፖለቲከኞችን ከውስጡ ለይቶ በማጋለጥና ሴራቸውን ይፋ በማድረግ ለሰላሙ መትጋት ይኖርበታል፡፡

እንደ እውነቱ ከሆነ የዚህን ጽሑፍ አቅራቢ ጨምሮ የማንኛውም እምነት አስተምህሮት ተከታታይ ምዕመን የሃይማኖት ልዩነት መኖሩ በማይታወቅበት ሁኔታ ውስጥ ተቻችሎ የመኖር ትውፊቱን ለጥቂት ጽንፈኞች አሳልፎ ይሰጣል ማለት የዋህነት ነው፡፡ ምክንያቱም በመቻቻሉና በመፈቃቀሩ ያተረፋቸው በሠላም ወጥቶ የመግባት እና በየደረጃው ከሚገኝ ልማታዊ ዕድገት ተጠቃሚ የመሆን… ወዘተ ትሩፋቶችን ማጣት አይፈልግምና፡፡ስለሆነም በሀገሩ ውስጥ የመኖር ዋስትናው የሆኑት እነዚህ ሁኔታዎችን ላለማጣት የመቻቻል ባህሉን ይበልጥ ማጎልበት እንደሚኖርበት መካሪ የሚያሻው አይመስለኝም፡፡

ለዚህ ደግሞ ፍቱን መድሃኒቱ የሃይማኖትን ጭምብል አጥልቀው የአክራሪነት ፖለቲካዊ አጀንዳን ከሚያራግቡ ጽንፈኞች ጀርባ ማን እንዳለ በትክክል በመርመር የግራና ቀኙን ምልከታዎች ማጤን ነው፡፡ እናም 'በአሁኑ ወቅት በእስልምናውም ይሁን በክርስትናው እምነት ውስጥ ተሰግስገው ተገቢ ያልሆኑ

ጥያቄዎችን ሃይማኖተኛ መስለው የሚያቀጣጥሉ ወገኖች እነማን ናቸው?፣ ሃይማኖቴስ የእምነት እኩልነትንና ነጻነትን ያጎናጸፈኝን ህገ - መንግስት ከሚሸረሽሩ ወገኖች ምን ያህል የጸዳ ነው?... ወዘተ' የሚሉ ጥያቄዎችን አንስቶ፤ ተገቢውን ምላሽ እየሰጡ ነባሩን የመቻቻልና የመከባበር ሃይማኖታዊ ባህል ያለ አንዳች እንከን ማስቀጠል እንደሚቻል ለዚህ ፅሁፍ አንባቢ ማውሳት "ለቀባሪው ማርዳት" ያህል በመሆኑ ግልፅ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ሁላችንም በየአምልኮ ቦታዎቻችን ከሃይማኖታችን ጋር ተያያዥነት የሌላቸውን የፖለቲካ ስብከቶች ሲኖሩ ማስቆም ይኖርብናል—ተግባሩ ፖለቲካዊ እንጂ ሃይማኖታዊ አይደለምና፡፡ እንዲሁም እያንዳንዳችን በራሳችን እምነት ውስጥ ምን ማድረግ እንዳለብን እንጂ፤ የሌላ ሃይማኖት ተከታዮች ምን ማድረግ እንዳለባቸው የሚያሳስቡ የጽንፈኝነት አመለካከቶችን ከወዲሁ "ሳይቃጠል በቅጠል" በማለት ሃይማኖታዊ ሰላምን ማስፈን ይኖርብናል፡፡

ሁሉም ሃይማኖቶች ሰላምን፣ ትዕግስትንና መቻቻልን የሚሰብኩ እንጂ፤ ሃይማኖትን በዋሻነት የሚጠቀሙ ጽልመተኞች እንደሚያራግቡት ጥላቻና ግጭትን የሚሰብክ ይዘት የሌላቸው መሆኑን ተገንዝበን ለጥፋት ኃይሎች በር መክፈት አይኖርብንም፡፡ ይህን ስናደርግም እንክርዳዱን የአመፃ ቡድን ከስንዴው ሰላማዊ ወገን መለየት እንችላለን፡፡

ያም ሆነ ይህ ግን፤ የሀገራችን ሃይማኖታዊ መቻቻል ምናልባትም "ወርቅ በእሳት ይፈተናል" እንዲሉ ያህል በጥቂቱም ቢሆን ሊፈተን ቢችልም፤ በጽልመተኞች ሴራ ግን ከቶም ቢሆን ሊደበዝዝ የሚችል አይደለም፡፡ ለምን ቢባል፤ ሃይማኖታዊ መቻቻላችን ስር የሰደደ ከመሆኑም በላይ፤ ሀገራችን እየተከተለችው ያለችው ህገ -መንግስታዊ ሥርዓት በሃይማኖት ሽፋን ግጭት ለሚፈጥሩ ወገኖች ምንም ዓይነት ስንዝር የጥፋት ቀዳዳ ስለማይፈጥር ነው፡፡ አዎ! አንድም ጋት እንኳን ቢሆን፡፡...